

### የተሻሻለ የወተት ከብቶች

# አያያዝ መመርያ

## የወተት ላሞች አያያዝ

2010 ዓ.ም

SNV

Designed & Printed by
master print
አራት ኪሎ ፡፡ +251 111 557 788 ገርጂ ፡፡ +251 116 298 777
31362 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
www.masterprintaddis.com

# 2 የወተት ላሞች አያያዝ

**የወተት ላሞችን ምርትና ምርታማነት ከሚወስኑ ዋና ዋና ግብዓቶች ውስጥ የመኖና መጠጥ ውሀ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ። የላሞች የመኖና የመጠጥ ውሀ ፍጆታ በዕድሜያቸው፣ ክብደታቸው እና ላሞች ያሉበት ሁኔታ (እንደ እርግዝናና የአለባ ሁኔታ) ይወሰናል።**



## ቁልፍ መልዕክት

የወተት ላሞች ምርትና ምርታማነት በዋናነት በዝርያቸው ዓይነት የሚወሰን ቢሆንም የሚከተሉት ተጨማሪ ምክንያቶች የራሳቸው ሚና አላቸው።

- የመኖ ጥራትና መጠን እንዲሁም የመጠጥ ውሀ አቅርቦት ሁኔታ
- የላሟ ጤንነት /በአካሏ ላይ ያሉ ችግሮች ለምሳሌ እንደ ማንከስ ያለ፣
- ከበረት ጋር ተያይዞ ያለ ምቾት፣ የአካባቢው የአየር ሁኔታ ምርታማ ላሞች ሙቀት አይችሉም
- በአለባ ሰዓት የሚደረጉ አስፈላጊ ተግባራት መኖርና አለመኖር፣ ይህም ማለት ላሟን ማለብ ከመጀመር በፊት ጡቶቹን ለብ ባለ ውሀ እና በፎጣ በማጽዳት እንዲነቃቃ ከተደረገ በኋላ መሆን አለበት፣
- ከግትና ጡቶች ጋር በተያያዘ የሚሠሩ ግቶችና ጡቶች ብዛት ለምሳሌ 2 ጡቶች ቢደፈኑ ከአጠቃላይ የወተት ምርት እስከ ግማሹ ይቀንሳል።

## 2.1 ለወተት ምርት አስፈላጊ የሆኑ ንጥረ ነገሮችና ምንጮቻቸው

**በእንሰሳት መኖ ውስጥ መካተት ያለባቸው ንጥረ ነገሮች፣ ሐይል ሰጪ፣ ኘሮቲን፣ ማዕድናት ቫይታሚኖችና ውሀ ናቸው።**

### ውሀ

- በእንሰሳት የሰውነት አሰራር ውስጥ ውሀ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። የአንድ ጥጃ ክብደት 3/4ው ውሀ ሲሆን በአንድ ላም አጠቃላይ ክብደት ግማሹ ውሀ ነው፣
- ለላሞች የሚያስፈልገውን የውሀ መጠን የሚወስኑ በርካታ ምክንያቶች አሉ። በመኖ ውስጥ ያለ የውሀ መጠን፣ ላሟ የተመገበችው ደረቅ መኖ መጠን፣ ላሟ የምትሰጠው የወተት ምርት መጠን፣ የአካባቢው ሙቀት መጠን፣ ላሟ የምትልሰው የጨው መጠን የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ።

### ሀይል ሰጪ

- ይህ ንጥረ ነገር ለወተት ላሞች በከፍተኛ መጠን የሚፈለግና የወተት አሰራርን የሚወስን ዋና ንጥረ ነገር ነው። ለአንድ ላም የሚያስፈልገው የሀይል ሰጪ ንጥረ ነገር መጠን በምትሰጠው የወተት መጠን ይወሰናል። በተጨማሪም እርግዝናና የላሞች እንቅስቃሴ የኃይል ሰጪ ንጥረ ነገር መጠንን ይወስናሉ።
- ምንጭ፡ አሰር አልባ መኖዎች /ኮንሰንትሬት/፣ የሳር ዘሮችና ቅጠላ ቅጠሎች፣ የብርዕ እህሎች፣ የእርሻ ተረፈ ምርቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ።
- የእጥረት ምልክቶች፡ የሐይል ሰጪ ንጥረ ነገር በመኖ ውስጥ በበቂ መጠን ከሌለ ላሟ ትከሳለች፣ የወተት ምርቷም ይቀንሳል።


### ኘሮቲን

- ኘሮቲን በሁለተኛ ደረጃ እጅግ ተፈላጊ ንጥረ ነገረ ነው። በወተት አሰራር ሂደት ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።
- ምንጭ፡ የቅባት እህሎች ጭማቂ /ፋጉሎ/፣ የአባዝር የመኖ ዓይነቶች /አልፋልፋ፣ ሌስምዲየም፣ የላም አተር የመሳሰሉት/፣ የተፈጩ የጥራጥሬ እህሎች /አተር፣ ባቄላ፣ ቦለቄ እና የቅንጠባ የመኖ ዓይነቶች (ሊውሲኒያ፣ የርግብ አተር፣ ሴስባኒያ የመሳሰሉት)።
- የእጥረት ምልክቶች፡ የወተት ምርት ፍጥነት ያሽቆለቁላል እንዲሁም የላሟ ክብደት በፍጥነት ይቀንሳል።

### ማዕድናት

- ማዕድናት ለላሞች በጣም አስፈላጊ የሆኑ ንጥረ ነገሮች ሲሆኑ አነስተኛ በሆነ መጠን ይሰጣቸዋል።
- ምንጭ፡ ጨው፣ የኖራ ድንጋይ/አፈር፣ የተለያዩ የመኖ ተክሎችና እህሎች ይጠቀሳሉ።

## 2.2 የወተት ላሞች ዋና ዋና የመኖ ዓይነቶች ስዕላዊ መግለጫዎች



የተሻሻሉ የመኖ ዝርያዎች



የበቆሎ አገዳ ለበጋ መኖነት



የእርሻ ተረፈ ምርት



ለበጋው ወቅት የሚከማች የእርሻ ተረፈ ምርት



ልቅ ግጦሽ



የተከተከት የሸንኮራ አገዳ



የእንሰት ተክል በበጋ ወቅት ለመኖነት



የቢራ ፋብሪካ ተረፈ ምርት

## 2.3 ለወተት ላሞች መኖ እና የመጠጥ ውሀ መጠን

**የወተት ላሞች የመኖ አመጋገብ ዘዴ የሚከተሉትን አራት ወቅቶችን የተከተለ ቢሆን ከወተት ከብቶች የሚገኘውን ጥቅም ከፍተኛ እንዲሆን ያደርጋል። እነዚህም:-**

1. **የሽግግር ወቅት**

- በእርግዝናዋ የመጨረሻ 21 ቀናት ቀደም ብሎ እና ከወለደችበት ቀን 21 ቀናት በኋላ /በድምሩ 42 ቀን ያለውን ጊዜ የሽግግር ወቅት እንለዋለን። ይህም የመጀመርያ ክፍል ነው።
- በዚህ ወቅት ከፍተኛ ኃይል ያለው ለምለም ሳርና ቅጠላቅጠል በሚገባ ሊፈጭ የሚችል ምጥን መኖ በበቂ ሁኔታ ያስፈልጋታል፣
- በዚህም በአመጋገብ ሥርዓት ሊደርሱ የሚችሉ የጤና ችግሮችን መቀነስ ይቻላል።
- ነገር ግን ላሟ እንደወለደች ባሉት ሦስት ቀናት ውስጥ ኮንሰንትሬት መኖ መመገብ ተገቢ አይደለም። ከዚህ ይልቅ በቂ ውሀ እና ቅጠላቅጠል መስጠት ተመራጭ ነው።

2. **የወተት ምርት ጣሪያ የሚደርስበት ወቅት** (**ከ2-4 ወር**)

- ይህ ወቅት የላሟ ሰውነት ክብደት በጣም የሚቀንስበት፣ የወተት ምርቷ በከፍተኛ ሁኔታ የሚጨምርበት ጊዜ ነው። ይህ ወቅት የላሟን የወተት ምርት ጣሪያ የምናውቅበት በመሆኑ የሚሰጣት መኖና ውሀ መጠን ይህንን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት።

3. **ከ4ኛ ወር እስከምትነጥፍበት ጊዜ**

- ይህ ወቅት የወተት ምርት ቀስ በቀስ የሚቀንስበት ጊዜ ነው። ላሟ የምትሰጠው የወተት መጠን ልክ የሚያስፈልጋትን የኮንሰንትሬት መጠን ቀስ በቀስ መቀነስ ይቻላል።

4. **የምትነጥፍበት ወቅት**

- ላሟ በዚህ ወቅት በፍጥነት እያደገ ያለ ሽል ስለሚኖራት ላሟን ማለብ አይገባም። በዚህ ወቅት የሚደረግ የአመጋገብ ዘዴ ላሟ ከወሊድ ጋር የሚገጥማትን ችግር ለመቀነስ፣ ከወለደች በኋላ የምትሰጠውን የወተት መጠን ከፍ ለማድረግ፣ የሽሉ እድገት እንዲፈጥንና ጤነኛና ጠንካራ እነዲሆን ያግዛል።

## ከ2.3 የቀጠለ

**1. ላሞች እንዴት እንዲነጥፉ ማድረግ ይቻላል?**

- ላሟ የሚሰጣትን የኮንሰንትሬት መጠን በመቀነስ፣
- የወተት ምርቷ ከፍተኛ ከሆነ የእርግዝናዋ ጊዜ ሊያልቅ አንድ ወር ተኩል ሲቀራት የወተት አለባ አንድ ቀን እየተዘለለ በማለብ በተከታታይ ባሉ ቀናት አለባ ማቆም፣
- የወተት ምርቷ አነስተኛ ከሆነ በቀጥታ አለባ ማቆም ይቻላል። ነገር ግን የጡት በሽታ እንዳያጋጥማቸው መከታተል ያስፈልጋል።

**2. ላሞች በወቅቱ እንዲነጥፉ ማድረግ የሚያስገኘው ጥቅም**

- ለግት በቂ ጊዜ በመስጠት እንዲያገግም በማድረግ ከወሊድ በኋላ የወተት ምርትን ከፍ ለማድረግ፣
- ለጥጃው /ሽሉ/ በቂ መኖ ለማትረፍ ጠንካራና ጤነኛ ጥጃ ለመውለድ፣
- ላሟን ከተለያዩ ድንገተኛ የበሽታ ችግሮች ለመከላከል፣

| የጥገቱ ዓይነት | የወተት ምርት መጠን (በቀን) | የውሃ መጠን (በቀን) |
|---|---|---|
| ጥጆች | - | ከ5-20 ሊትር |
| ጊደሮች | - | ከ20-50 ሊትር |
| ታላቢ ላሞች | ከ10 ሊትር | ከ65-100 ሊትር |
| ታላቢ ላሞች | ከ10-20 ሊትር | ከ100-145 ሊትር |
| ታላቢ ላሞች | ከ20-30 ሊትር | ከ145-185 ሊትር |
| የነጠፈች ላም | - | ከ65-75 ሊትር |



## 2.4 ለወተት ላሞች የሚሰጥ የአሰር-አልባ (ኮንሰንትሬት) እና አሰር-በዝ (ራፌጅ) አመጣጥኖ መስጠት

**የአሰር-አልባ (ኮንሰንትሬት) እና አሰር-በዝ (ራፌጅ) የመኖ መጠን ማወቅና በዚህ መሠረት መመገብ የላሞች ጨጓራ ውስጥ ያለን የፍጭት ሥርዓት/ሂደት እንዳይዛባና፣ አላስፈላጊ ወጪ እንዳያስከትል እና የወተት ምርትና ምርታማነትን ከፍ እንዲል ለማድረግ ያስችላል።**

# ቁልፍ መልዕክት

- የአሰር-አልባ መኖ መጠን ላሞችን በመመገብ የወተትን ምርት ማሻሻል ይቻላል ። ነገር ግን የአሰር - አልባ መጠን ከ1/5ኛ በላይ ከሆነ አዋጪ ላይሆን ይችላል፣
- የወተት ከብት አርቢዎች በቂ መሬት ካላቸው የተሻሻሉ መኖ ተክሎችን በመትከልና በመመገብ አላስፈላጊ ወጪን መቀነስ ይችላሉ።



